# ውሀ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው!

ከተስፋዬ መኮንን

July 1, 2017

የትግሬ ነጻ አውጪ ነኝ ባዩ የአዲስ አበባን ህልውና አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ አነጋጋሪ ሁኗል። በመሰረቱ በጉዳዩ ላይ የሚነጋገሩትን ከሁለት መክፈል ይቻላል። የመጀመሪያው የቁጭትና የእንዴት ይሞከራል ቡድን ነው። ሌላው ውሀ እያሳሳቀ ይወስዳል እንዲሉ በገደምዳሜ ሳይታወቀው እቃወመዋለሁ ለሚለው ለወያኔ ህገ መንግስት እውቅናን በመለገስ "ኦሮሞ በአዲስ አበባ ላይ ሊኖረው በሚገባ ልዩ ጥቅም ስር ተጠልሎ የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን እንደገና በመመለስ መሬት ለመዝረፍ ወያኔ ያሴረው ሴራ ነው" የሚለው ነው።

እኔ የማተኩረው ሁለተኛው ሀሳብ ላይ ነው። በመሰረቱ ወያኔ ከዚህ በመጨረሻ ሰአት ላይ በጭንቅ ከጣላውና ወደፊትም ሊጥል ከሚችላቸው ማደናገሪያዎቹ ላይ ተነስተን "ይህን ፈልጎ ነው" ብለን አቋም ስንሰነዝር ከዋናው መሰረታዊ አቋማችን እንዳናፈነግጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል። ወያኔ በማወቅም ይሁን ሳያውቅ አንድ አዋጅ ሲማታ አዋጁ በተጓዳኝ ሊያመጣለት የሚችሉ አጫፋሪ ጥቅማጥቅሞችን ታሳቢ ሊያደርግ ይችላል። ይሁንና የአዋጁን እምብርት ግን ይስተዋል ማለት አይደለም። ከእኛም ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነትና ለሀገር ሉአላዊነት ቁመናል ከምንል በወያኔ አዋጅ ውስጥ እምብርቱ ጥያቄ የቱ ነው? አጫፋሪዎቹ ጥያቄዎቹስ? ብለን የመለየት ተግባር የጠበቃል።

ከአዋጁ ቃድሞ የመጣ የወያኔ መግለጫ የህዝቡን ስሜት ለማንበብና ለመለካት የመጣ መሆኑ ግልጽ ነው። ዋናው የአዋጁ እምብርት ግን በተቃዋሚው ጎራ ተፈራርቶ የተቀመጠውን የፖለቲካ ባላንጣ ገፍቶ ሚናውን እንዲለይ ለማድረግ ነው። አላማው "ኦሮሞ (ኦነግ ማለት ይሻላል) በአዲስ አበባ ላይ የሚኖረውን መብት" በሚደግፉና በሚቃወሙ መሀል ተከፍሎ ሚናውን እንዲለይ ለማድረግ ነው። በሌላ አነጋገር በዚህ ቆስቋሽነት በሚነሳ ንትርክ በኦነግ ተረቆ ለ 26 ዓመታት በወያኔ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ላለ የጎጥ ህገመንግስት እውቅና በሚሰጡና በማይሰጡ መሀል ግልጽ አቋም የያዘ ወገነ- ወያኔ የሆነው ለይቶለት እንዲቀላቀለው ምኞት የሰነቀ መግለጫ አዋጅ ነው።

በመሰረቱ በአንድነት ሀይሎችና በተገንጣይ ሀይሎች መሀል ይህ አቋም ግልጽ ሁኖ የቆየ ነው። ይሁንና ግልጽነቱ ግን በንድፈ ሀሳብ ብቻ የነበር ነው። በሁለቱ መሀ ግብ ግብ የሚያስገጥም የጦር ሜዳ አልነበረም። አሁን ወያኔ ለመጠየቅ የፈለገው በግልጽ አቋም ተወስዶ ከወያኔ ጋር የአቋም ተመሳሳ ካላቸው ጋር በተግባር ለመቀራረብ ያለውን ፍላጎቱን ያሳየበት ነው። ዓላማው ይህ ባይሆን ኖሮ ወያኔና ኦነግ የተስማሙበትን የዝረፍ እንዝረፍ ስምምነት ለ 26 አመታት በሳጥን ውስጥ ማስቀመጥ ባላስፈለገ ነበር። በጭንቅ ጊዜ የሚመዘዝ ወዳጅ መግዢያ ሆኖ የተቀመጠ መርዝ ነበር። ዛሬ ጊዜው ለወያኔ የምጥ ጊዜ ስለሆነ ከቀድሞ ወዳጁ ጋር እንደገና ለመቀራረብ ይህንን መርዙን ይዞ ብቅ አለ። ይህንን ማድረግ ይጠበቅበታል። ከእንግዲህ መጠየቅ ያለበት በተለያየ መሸፋፈኛ የተኮለኮሉ ኦነጋውያንና አጋሮቻቸው ለምን ጎዞ ወደ "ፍንፊኔ" እንደማያደርጉ ነው። በነሱና በወያኔ መሀል ያለው አቦ ስብሀት "ልዩነታችን የወንበር ነው" ያለው ትክክል ነው። የወንበር ድርድር ማድረጊያውና ሳያጠፋቸው ላይመለስ የተነሳውን የጋራ ጠላት የመቋቋሚያው ጊዜ ዛሬ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝብ ልታውቀውና ልትጨብጠው የሚገባ የመግለጫው እምብርት ወያኔ ያንተን ትግል ለማፈን ለኦነግና አብረውት ለሚያጫፍሩት የተደረገ የእንተባበር የትግል ጥሪ መሆኑን ነው።

በመግለጫው ውስጥ በተጓዳኝ የመጡ ጭፍጫፊና አጫፋሪ የሆኑት የሚከተሉት ናቸው።

1. ቋንቋ፥ የኦሮምኛ ቋንቋ የአዲስ አበባ የስራ ቋንቋ ይሆናል፣ የባህል ተቋሞች፣ ት/ ቤቶች ይገነባሉ፣ የጎዳና ስያሜ ይደረግልሀል፣ የከተማው መጠሪያ "ፊንፊኔ" ይባላል፣ ወዘተ ለሕጻናት ከረሜላ እንደመበተን የሚታየው ማፈሪያ ነው። በመሰረቱ ከወያኔ ጋር ይሉይታና ማፈር አብረውት አልተሰሩም።

በመሰረቱ የኦሮምኛ ቋንቋ የኢትዮጵያ ህዝብ ቋንቋዎች ውስጥ ከአንጋፋዎቹ አንዱ ነው። የቋንቋው ባለቤት የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ። እናም ብሄራዊ የሀገሪቱ የመስሪያ ቋንቋ ይሁን አይሁን ወሳኙ ባለቤቱ ህዝቡ ነው። ህዝቡ የሚጠቀመውን ያውቃል። የቋንቋ ጥያቄ የህዝቡ የእድገት አስፈላጊ ጥያቄ ነው። ለእድገቱ ይበጀኛል ብሎ ሲወስን ከቋንቋዎቹ ውስጥ መርጦ የብሄራዊ መገናኛው ሊያደርገው ይችላል። ለዚህ መሰሉ ብሄራዊ ተግባር ከኦሮሞ ቋንቋ በተጓዳኝ ዓለም አቀፍ ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ቋንቋዎቻችንንም የኢትዮጵያ ልጆች በትምህርት ገበታ ላይ በምርጫ እንዲማሩ ቢደረግ ትክክል ይሆናል። ለምሳሌም አፋርንና የሱማሌ ቋንቋዎቻችንን። ለዚህ ወያኔም ሆነ ኦነግ ተብዬ የሚያገባቸው ነገር የለም። በዚህ የራሳችን በሆነ ጉዳይም እኛን መልሰው ሊያስፈራሩን አይችሉም። ህዝቡ ለሚናገርባቸው 87 ቋንቋዎቹ መዳበር፣ ማደግ፣ መስፋፋታን እያንዳንዱ የሁሉም እንዲሆን የመስራት መብቱን የሚያረጋግጠው በስሙ ከፋፍለውት የደለቡ ፊሺሽቶች ከራሱ ላይ ሲወርዱ ይሆናል።

የኦሮምኛ ቋንቋችን የአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ዲሞክራሳዊት ኢትዮጵያ ስትመሰረት በህዝቡ ውሳኔ በሚመሰረት የሸዋ ክ/

ሐገር መስተዳድር ከአማርኛ ጎን የክ/ሐገሩ ቋንቋ እንዲሆን የምንታገልለት ግባችን ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ወያኔና አነግ የተከሉት በጎሳ ላይ የተመሰረተ የመሬት ይገባኛል ፖለቲካንና የሱ ውጤት የሆነውን የጎሳ ያጥር ክልል ሰባብረን ሳንጥል በሰው የግል ነጽነት ላይ የተመሰረተ የህዝብን አንድነት እውን ማድረግ አንችልም። በዚህም መሰረታዊ ምክንያት ነው "የኦሮምያ ልዩ ዞን፣ የኦሮምያ ልዩ ጥቅም፣ ወዘተ " ተብዬዎችን በአጀንዳችን ላይ ቦታ የማንሰጣቸው።

አዲስ አበባ አንድና አንድ ስም ነው ያላት። ባለቤትነቷም የ 87 የቋንቋ ማህበረሰቦቿ ነው። የገነቧትም፣ እየገነቧት ያሉትም ሁሉም በአንድነት ነው። ያለችውም በኢትዮጵያ እምብርት ላይ ነው። የኢትዮጵያ መሬትም የመላው ህዝብ የጋራ ሀብት ነው ። እናም በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የከተማዎቿ መሬት የትግሬም፣ የኦሮሞም፣ የአማራም፣ ወዘት የብቻ የጎሳ መሬት አይደለም። የከተሞቹ የህዝብ ስብጥርም የመላው ህዝቧ ስብጥር ነው። ሲሰፋ የሸዋ ክ/ ሐገር ሲጠብም የአዲስ አበባ ባህሏም፣ መልኳም፣ ውበቷም፣ ትውልዷም ድቅልቅል ያለ፣ ውበቷም ማራኪ የሁላቸውም መግለጫ ናት። ከተማነቷም የሸዋ / ሀገር፣ የኢትዮጵያ፣ የአፍሪካና የዓለም ዋና ከተማ ናት። ወደፊትም በትግላችን የምናጠናው ይህንን ነው። ከጎሳዎቿ ውስጥ ማንኛቸውም የግሌ ናት የሚያስኝ መነሻ ታሪክ የለውም። ኢትዮጵያና አዲስ አበባ የተሰሩት በሁሉም ህዝቧ ነው።

2. ሌላው በመግለጫው ውስጥ እንደጭፍጫፊ የሚታየው በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለውን የገበሬውን መሬት ሊዘርፉት ነው የሚለው ነው። በመሰረቱ ለምን የአዲስ አበባ ዙሪያ ያለው ገበሬ በደል ተነስቶ በአዲስ አበባ ውስጥ ያለው በግሬደር የሚታረስ ቤት እንዳልተጠቀሰ ነው የሚገርመው። ትንታኔያችን መነሻውም መድረሻውም ጎሳ በመሆኑ ተመልሰን በወያኔ ወጥመድ ውስጥ እንወድቃለን ። በከተማዋ ዙሪያ ያሉት ገበሬዎችም ሆኑ የከተማዋ ድሀ ህዝብ ሰለባ የሆኑት በወያኔ ነው። ልንሟገት የሚገባን ለሁሉም ነው። ዘረፋውም የወያኔ ልዩ መግለጫ ናውና ክ/ ሐገራትን ቆርሶ ለትግሬ ታላቅነት፣ ገቤሬውን አባሮ ሁዳድ ማራስና ማሳረስ፣ ለመዛመድም ግዛትን ቆርሶ ለባእድ ሀገር መስጠትን ያካተተ ወንጀል እንዳለ እንዴት ይዘነጋል? በቅድሚያ በወያኔ ላይ መሬት የያዘ ተቃውሞም ሆነ ግምገማ ለማድረግ ከወያኔ ህገመንግስት ተብዬ ጋር መቆራረጥን ይጠይቃል። ለዚህም ነው ዋናውን የጥያቄውን ግንድ ሳናይ ቅርንጫፎቹን የምንመለከት። ኢትዮጵያዊው ኦሮሞ ለቅንጣቦ ስጋ አይታገልም።

ለማጠቃለል ማለት የሚቻለው ወያኔ በመውደቂያው አፋፍ ላይ ነው ያለው። የመጨረሻው ቀን መምጣቱን ተረድቷል። የማይለቅ ጠላት ከሰሜን፣ ከመሀልና ከደቡብ ተነስቶበታል። ለዚህ የመጨረሻ ግብግብ ትናንት በእብሪት ከዘረፋው ማእድ ላይ ያባረራቸውን ለመመለስ ማባበያ እጁን ቢዘረጋ ለምን እንዲህ አደረክ አይባልም። መሰሎቹ ሁሉ በዚያ የመሸ አጭር ጎዳና ውስጥ ሲገቡ ያደረጉት ነው። ነገ በግልጥ አብረውት የሚቆሙትን ደግሞ ሳናይ እንዳናልፍ መጠለይ ነው።

በሰሜን፣ በመሀል፣ በደቡብና በምእራብ ወምስራቅ ከተቀጣጠላው የህዝባችን ትግል ጋር እንቁም!

በምንችለው ከመርዳት ወደኋላ አንበል!

ኢትዮጵያ ከእውነተኛ ልጆቿ ጋር ወደፊት!